በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና ግንባታ

ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

የአሰራር መመሪያ 1/2011

መጋቢት 2011

ማውጫ

መግቢያ 1

ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ 2

1. አጭር ርዕስ 2
2. ትርጓሜ 2
3. የተፈጻሚነት ወሰንና መመሪያ ማሻሻል 5

ክፍል ሁለት፡ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ 6

4. አጠቃላይ 6
5. የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻ አቀራረብ 6
6. የፕላን ማስገምገሚያ ጊዜ 7

ክፍል ሶስት፡ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር 9

7. አጠቃላይ 9
8. መደበኛ ክትትል 9
9. ድንገተኛ ክትትል 10
10. ግንባታ ቁጥጥር 11

ክፍል አራት፡ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ 12

11. አጠቃላይ 12

ክፍል አምስት፡ በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች 13

12. አጠቃላይ 13

ክፍል ስድስት፡ የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠርና ልዩ ልዩ 14

13. የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር 14
14. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር 14
15. የተመዘገቡ አማካሪዎችን ስለመቅጠር 14
16. መመሪያውን ስለማሻሻል 14
17. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ 14

መግቢያ

በከተማችን በመካሔድ ላይ ያለው የግንባታ ሥርዓት ባለው እና ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲመራ ለማድረግ፣ የሕዝብን ጤንነትና ደህንነትና ብልጽግና ለማረጋገጥና በመዲናይቱ ተፈፃሚነት የሚኖረው ምቹ የግንባታ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እንዲሁም የግንባታ የሥራ ሂደቶችና ዝርዝር አፈፃፀም ለአገልግሎት ሰጪም ሆነ ለተገልጋዩ ግልጽ በማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ተጠያቂነት ያለበት የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት ይህንን ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

መንግስት የንግድና ኢንቨስትመንት ተቋማትን በልዩ ሁኔታ ለማበረታታት የሚያካሂዳቸውን ተግባራት ግቡን ይመታ ዘንድ ለዚሁ ተግባር የግንባታ ፍቃድ፣ቁጥጥርና ክትትል አሰጣጥ የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርዶችን፤ አገልግሎት ለማግኘት ወደ ባለሥልጣኑ የሚመጡ ደንበኞችን መብት፣ተግባር እና ሃላፊነት በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ለማውጣት እና ለማስፈፀም በከተማው አስተዳደር በተሰጠው ሥልጣንና በከማተው አስተዳደር የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15.3(ሠ) በተደነገገው መሠረት እንዲሁም የኢትዮጵያ ህንፃ አዋጅ 624/2001፣የኢትዮጵያ የህንፃ ደንብ 243/2003 ፣የህንፃ መመሪያ ቁጥር 5/2003 እና የአዲስ አበባ የህንፃ መመሪያ 2/2010 መሰረት በማድረግ ይህ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የአሰራር መመሪያ ቁጥር 1/2011 ተብሎ በመሰረተ ልማት ቅንጅትና ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ወጥቷል፡፡

ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሰረተ ልማት ቅንጅት፣ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የግንባታ ፈቃድ፣ ክትትልና መጠቀሚያ ፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 01/2011ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ፍቺ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1. "ከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዉ፤

2.2."ባለስልጣን" ማለት የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

2.3."ጽ/ቤት" ማለት በክ/ከተማና የወረዳ መሰረተልማት ቅንጅትና ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ጽ/ቤት ነው፡፡

2.4. "የፕላን ስምምነት" ማለት ስልጣን ባለው አካል ለህንጻ ግንባታ የቀረበ የግንባታ ዲዛይን/ፕላን ከከተማዉ ፕላን ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ስምምነት ነዉ፤

2.5."ግንባታ":- ማንኛውም ከመሬት በታች፣ከመሬት ላይ እና በላይ የሚገነባ አዲስ ህንጻ፣ መጠለያ፣ አጥር፣ የመሰረተ ልማት አውታር እንዲሁም ነባር ህንጻ ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ማለት ነው፡፡

2.6."የግንባታ ዲዛይን/ፕላን"፡-የአንድን ሕንፃ መጠን ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃ የሚሰራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴ የማያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የእስትራክቼር፣ የሳኒቴሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ መካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችንም ንድፍ ሊያካትት ይችላል፡፡

2.7."ገንቢ"፡-ማለት የግንባታ ደረጃውን የሚመጥንና ግንባታውን ለመስራት ውል የወሰደ የሥራ ተቋራጭ ወይም ለአነስተኛ ግንባታዎች ግለሰብ ባለሙያ ወይም ባለሙያ የሆነ የግንባታው ባለቤት ነው ፤

2.8.“የሕንፃ ሹም”፡- ማለት የህንጻ አዋጁን የማስፈጸሚያ ደንቡን እና ይህንን መመሪያ የሚያስፈጽም በከተማው አስተዳደር በተሰየመ አካል የተሾመ ሰው ማለት ነው፤

2.9.“ሪል እስቴት”፡- ማለት ለሽያጭ፣ ለኪራይ፣ ወይም ለሊዝ አገልግሎት እንዲውል የተገነባ የመኖሪያ ሕንጻ ነው።

2.10.የህንጻ ምድብ፡- ማለት የሕንጻ ከፍታ እና የህንጻ አገልግሎት ባህሪይ ብቻ ለመግለጽ የሚጠቅም ስያሜ ሲሆን የህንፃው አገልግሎት ከተጠቀሰ የህንፃውን ቁመት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ምደባው ሊከናወን ይችላል ፤

2.11."ምድብ "ሀ" ሕንፃ "፡-ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለ አንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው፤

2.12."ምድብ "ለ" ሕንፃ "፡-ማለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ከ7ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ "ሐ" የማይሸፈን ሕንፃ ወይም "ምድብ "ሀ" የተመደበ እንደሪል እስቴት ያሉ የቤቶች ልማት ነው፤

2.13."ምድብ "ሐ" ሕንፃ" ፡- ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ ፣የፋብሪካ ወይም የወርክ ሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታ ከ12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ የተካተቱትን ማስተካከያዎች ያካትታል፤

2.14.“የሕዝብ መገልገያ ሕንፃ”፡- ማለት ከግል መኖሪያ ሕንፃ ውጪ የሆነ ማንኛውም ሕንፃ ነው፤

2.15."የወለል ብዛት"ማለት ከመሬት በታች፣መሬት ላይና ከመሬት በላይ ያሉ የቆጥ ወለሎችን ሳይጨምር አንድ ግንባታ ያሉት አጠቃላይ የወለል ብዛት ማለት ነው፤

2.16."አስጊ ህንፃ" ማለት ግንባታው አስተማማኝ ያልሆነ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ለእሳት አደጋ የተጋለጠ ወይም ለጤና ጠንቅ የሆነ ህንፃ ነው።

2.17.″የሕንፃ ተቆጣጣሪ″ ማለት በሕንፃ ሹሙ ሥር በመሆን በከተማው አስተዳደር ክልል የሚካሄዱ ግንባታዎችን ሕጋዊነትና የተሰጠውን ፈቃድ በሚመለከት በቅርብ የሚቆጣጠር ባለሙያ ማለት ነው፤

2.18."መደበኛ ክትትል" ማለት ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ህጋዊ የግንባታ ፈቃድ ያላቸውን ግንባታዎችበተፈቀደለቸው ግንባታ ፈቃድ መሰረት ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ ግንባታው ላይ መደበኛ ክትትል ማድረግ ማለት ነው፤

2.19."ድንገተኛ ክትትል" ማለት ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ህጋዊ የግንባታ ፈቃድ ያላቸውን ግንባታዎች በተፈቀደላቸው ግንባታ ፈቃድ መሰረት እየገነቡ ሰለመሆናቸው የሚደረግ ድንገተኛ ክትትል ማለት ነው፤

2.20."ስጋትን መሰረት ያደረገ ድንገተኛ ክትትል" ማለት ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ህጋዊ የግንባታ ፈቃድ ያላቸውን ግንባታዎች የስጋት መጠን በመወሰንና መሰረት በማድረግ የሚደረግ ድንገተኛ ክትትል ማለት ነው፤

2.21."የመጨረሻ ቁጥጥር" ማለት ግንባታው የተጠናቀቀና የመጠቀሚያ ፍቃድ ለማግኘት ማመልከቻ በቀረበበት ህንፃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር ነው፤

2.22."የተመዘገበ ባለሙያ"፡- ማለት ማንኛውም በሰለጠነበት የዲዛይን ወይንም የኮንስትራክሽን ስራ እንዲሰማራ የመመዝገብ ስልጣን ባለው አካል የተመዘገበና ለዘመኑ የታደሰ የባለሙያ ምስክር ወረቀት ያለው ሰው ነው፤

2.23. "የሕንፃ አዋጅ"፡- ማለት የኢትዮጵያ ሕንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ነው፤

2.24."የሕንፃ ደንብ"፡ማለት የሚኒስቴሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 243/2003 ነው፤

2.25."መመሪያ"፡- ማለት የህንፃ ደንብን ለማስፈፀም የወጣ የፌደራል የህንፃ መመሪያ 5/2003 (ከነማሻሻያው) እና የአዲስ አበባ የህንጻ መመሪያ ቁጥር 2/2010ነው፤

2.26."ሰው"፡ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

2.27."ስታንዳርድ"፡- ማለት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርድ ወይም ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ስታንዳርድ ነው፡፡

*በዚህ መመሪያ ላይ የሌሉት ትርጓሜዎች በኢትዮጵያ የህንጻ አዋጅ ደንብና መመሪያ እንዲሁምስታንዳርዶች መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰንና መመሪያ ማሻሻል

3.1 ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል

ሀ. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ በማንኛውም ግንባታ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ለ. ይህ መመሪያ ከመጋቢት-----ቀን 2011ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ሐ. ይህንን መመሪያ የማሻሻል ሥልጣን የመሰረተ ልማት ቅንጅት እና ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

3.2 ይህ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፣

ሀ. አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ላይ በሚገኝ በማንኛውም ሕንፃ፣

ለ. ከሀገር ደንነት ጋር በተያያዘ የሕንፃ አዋጁ ተፈፃሚ እዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰኑ ሕንፃዎች ላይ፣

3.3 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3.2 ድንጋጌ ቢኖርም፣

ሀ. አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የህንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታ አዋጁ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

ለ. አዋጁ ከመጽናቱ በፊት የተጠናቀቀና አዋጁ ከፀና በኋላ የአገልግሎት ለውጥ፣ የማስፋፋት ወይንም የማፍረስ ጥያቄ በሚቀርብበት ሕንፃ ላይ የከተማው አስተዳደር ወይም የተሰየመው አካል ተፈፃሚ እንዲሆንበት ማድረግ ይችላል፡፡

ክፍልሁለት፡ ግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ

4. አጠቃላይ

4.1. የማንኛውም ግንባታ ዲዛይን ሁሉንም የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶችን፣ የህንፃ አዋጅ፣ የህንፃ ደንብ እና የህንፃ መመሪያን ያሟላና የህንፃውን ተጠቃሚና የአካባቢውን ማህበረሰብ ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት።

4.2. የህንፃ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንበት ማንኛውም በከተማ ውስጥ የሚካሔድ የህንፃ ግንባታ በቅድሚያ የግንባታ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

4.3.የግንባታ ፈቃድ በግንባታው ባለቤት ወይንም በህጋዊ ወኪል ወይንም ንድፉን ባዘጋጀው አማካሪ ወይንም ባለሙያ አቅራቢነት ብቻ መካሄድ ይችላል።

4.4.በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ ነገር ግን አንድ አይነት ስታንዳርድ ፕላን ያላቸው ግንባታዎች የየራሳቸው የግንባታ ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል።

5. የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ማመልከቻ አቀራረብ

5.1. አዲስ፣ተጨማሪ እና የማሻሻያ ግንባታ ለማከናወን እንዲሁም ከግንባታ የተወሰደ (As-Built) ፈቃድ የሚፈልግ ሰው የህንፃውን ዲዛይን ከማዘጋጀቱ በፊት የፕላን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፤

5.2. የፕላን ስምምነት ግንባታው ከሚከናወንበት ክፍለ ከተማ ወይንም የግንባታ ፈቃዱ ከሚሰጥበት የባለስልጣንመ/ቤት ከ45 ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መውሰድ ይቻላል፤

5.3.የፕላን ስምምነት ለማግኘት በቅድሚያ በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ማመልከቻ ተሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል፣እንዲሁም የሚሰጠው የፕላን ስምምነት በከተማው መሪ ፕላን ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፣

5.4. በባለሥልጣኑ የማዕከል፣የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚሰጡ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎቶች ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ይህን መመሪያ፣የሕንፃ ደንቡንና የሕንፃ አዋጁን ድንጋጌዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ መሠረት በማድረግ ይከናወናሉ፤

5.5.የግንባታ ዲዛይን/ ኘላን በሚቀርብበት ወቅት ማሟላት ያለባቸውን ማስረጃዎች አሟልተው መቅረብ አለባቸው እንዲሁም የሚቀርቡት ዲዛይኖች የሚቀርቡ ፕላኖች መዘጋጀት የሚኖርባቸው በዲዛይን ባለሙያዎች እና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያ መሠረት

የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚያሟሉና እና ባለሙያዎችን ለመመዝገብና ለመፍቀድ ሥልጣን በተሰጠው አካል በተመዘገቡ ባለሙያዎች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5.6.የግንባታ ዲዛይን (ፕላን) ግምገማና ማጽደቅ የሚያከናውኑ ባለሞያዎች በአዋጅ 102/2010 እንዲሁም በባለስልጣን መ/ቤቱ የሰራተኛ ምደባ መስፈርት መሰረት የተቀመጡ የምዝገባ ፣የትምህርት እና የልምድ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

5.7.ከኢትዮጵያ ውጪ ዲዛይን ተደርገው የሚቀርቡ ዲዛይኖች በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ህጎችና መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፤

5.8.የአማካሪ ድርጅቱ የሚቀርበውን አርክቴክቸራል ዲዛይን የአርክቴክቸራል ዲዛይን እርማት መስጫ መስፈርቶች (ቼክ ሊስት 1) መሰረት መሰራቱን በቅድሚያ በማረጋገጥ የድርጅቱን ማህተብ በማድረግ ያቀርባል፤

5.9.የተሰጠውን እርማት ያልተቀበለ አማካሪ ዲዛይኑን ከመረመረው ባለሙያ ጋር በመቅረብ ተጨማሪ ማብራሪያ ወይንም አስተያየት መጠየቅና መረዳት ይችላል፤ እርማት የሰጠውም ባለሙያ ያልተሟላውን የመዋቅራዊ ፕላን፣ የህንፃ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ወይንም የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ በመግለፅ መልስ ይሰጣል፤

5.10.አንድ ዲዛይን ከሶስት ዙር በላይ የማይታረም ሲሆን በሶስተኛው እርማት መሰረት ተስተካክሎ ካልመጣ ዲዛይኑ ውድቅ ይደረጋል ፤

5.11.አንድ ዲዛይን ከሶስት ዙር በላይ የማይታረም ሲሆን በሶስተኛው እርማት መሰረት ተስተካክሎ ካልመጣ ዲዛይኑ ውድቅ ተደርጎ የዲዛይን መገምገሚያ ሙሉ ክፍያ 25% በማስከፈል በሌላ ባለሙያ እንዲገመገም ይደረግል፤

5.12.የግንባታ ፍቃድ ማመልከቻ በሚቀርብበት ወቅት በቅፅ 1 በተራ ቁጥር 1.1፣ 1.3፣ 1.5፣1.6፣ 2.1፣ 2.2፣ 2.3፣ 2.4፣ 3.1፣ 3.2 እና 4.1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት ተጨማሪ ሰነዶች የአርክቴክቸራል ዲዛይን ከፀደቀ በኃላ መግባት ይችላሉ፡፡

5.13.ማንኛውም ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርብ ዲዛይን በህንፃ መመሪያ 2/2010 በአንቀጽ 3.3 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

6. የፕላን ማስገምገሚያ ጊዜ

6.1.ማንኛውም ለግንባታ ሥራ የተዘጋጁ ፕላኖች በመመሪያው ላይ በተገለፀው መሰረት ለየሕንጻ ምድቡ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መገምገም አለባቸው፣ሆኖም በመመሪያው ላይ ከተገለፀው ቀን ባጠረ ጊዜ አገልግሎቱን ለመስጠት የአርክቴክቸራል ዲዛይን ከፀደቀ በኂላ ቀሪ ዲዛይኖች አንድ ላይ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

6.2.ለአንድ የሕንጻ ዓይነት የተዘጋጁ የግንባታ ዲዛይኖችን/ፕላኖችን ለመገምገም በአማካኝ የሚያስፈልገው ጊዜ ፤

ሀ. ከሪልስቴት ውጪ ላለ በምድብ "ሀ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ5 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣

ለ. በምድብ "ለ" ስር ለሚካተት ሕንፃ የኘላኖች መገምገሚያ ጊዜ ከ10 የሥራ ቀናት ያልበለጠ፣

ሐ.በምድብ "ሐ" ስር ለሚካተት ሕንፃ እና በምድብ "ለ" ውስጥ ለሚካተቱ የሪል እስቴት ህንጻዎች ኘላኖች የመገምገሚያ ጊዜ ከ13 የሥራ ቀናት የበለጠ መሆን የለበትም፡፡

6.3.በህንፃ መመሪያ ቁጥር 2/2010 የተገለፀው የዲዛይን /ፕላኖች መገምገሚያ ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ የመገምገሚያ ጊዜውን ለማሳጥር እና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ከታች በሰንጠረዥ በተገለፀው አግባብ ተስተካክሎ ቀርቧል፡፡የአርክቴክቸራል ዲዛይን ከፀደቀ በኋላ ቀሪ ዲዛይኖች አንድ ላይ ሲገቡ ከታች በሰንጠረዡ እንደተገለፀው ይሆናል፡፡

ተ.ቁ	የግንባታው አይነት	የወለል ስፋት	የይዞታ ስፋት በሜ.ካ.	ለምርመራ የሚፈጀው ከፍተኛ ቀን					
				አርክቴክቸራል	ስትራክቸራል	ኤሌክትሪካል	ሳኒተሪ	መካኒካል	ድምር
1.	ነጠላ መኖሪያ ቤት	1	ማንኛውም	2	-	1	-	-	3
2.	ነጠላ መኖሪያ ቤት	≥2	"	3	2				5
3.	የህዝብ መጠቀሚያ ህንጻ	ማንኛውም	"	8	5				13
4.	ማምረቻና ማከማቻ	"	"	8	5				13

6.4.ከፕሮጀክቱ ስፋት ወይም ውስብስብነት የተነሳ ተጨማሪ ጊዜ ለሚሹ ስራዎች የህንጻ ሹሙ ለከተማ አስተዳደሩ ወይም ለተሰየመው አካል ለፕላን ግምገማ ተጨማሪ ጊዜ ቅጽ 24 በመሙላት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

6.5.የሃይማኖት ተቋማት፣ ዲፕሎማቲክ ተቋማት እና አገራዊ ፋይዳ ያላቸው ግንባታዎች፣ በመንግስት ባለቤትነት የሚተዳደሩ ግንባታዎችቅድሚያ ተሰጥቶአቸው ይስተናገዳሉ፤

ክፍል ሶስት፡ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር

7. አጠቃላይ

7.1.ማንኛውም የግንባታ ማስጀመሪያ የሚፈልግ ሰው ወይም አካል በህንፃ መመሪያ 2/2010 አንቀጽ 14 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

7.2.ማንኛውም የህንፃ ግንባታ የሚያደርግ ሰው ወይም አካል ሁሉንም የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶችን፣ የህንፃ አዋጅ፣ የህንፃ ደንብ እና የህንፃ መመሪያን ያሟላና የሰራተኛውንና የአካባቢውን ማህበረሰብ ደህንነት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

7.3.የክትትልና የቁጥጥር ስረዎችን የሚያከናውኑ ባለሞያዎች በአዋጅ 102/2010 እንዲሁም በባለስልጣን መ/ቤቱ የሰራተኛ ምደባ መስፈርት መሰረት የተቀመጡ የምዝገባ ፣የትምህርት እና የልምድ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

7.4.ማንኛውም በከተማው አስተዳደር ወይም በተሰየመ አካል ማንነቱን የሚገለጽ መታወቂያ የያዘ የግንባታ ሥራ ተቆጣጣሪ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ወይም ግንባታ በሚከናወንበት በማንኛውም ጊዜ በግንባታው ቅጥር ግቢ ተገኝቶ የቁጥጥር ሥራ በማከናወን ቅጽ 13 በመሙላት ለሕንጻ ሹሙ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል ፣

7.5.የሕንጻ ተቆጣጣሪው የሕንፃ አዋጁን፤ ደንቡና መመሪያውን እንዲሁም ተጓዳኝ ሕጐች በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ ቅጽ 015 በመሙላት እንዲቆም ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

8. መደበኛ ክትትል

8.1.ማንኛውንም በምድብ "ለ" እና "ሐ" የሚገኝ ሕንፃ (ከግል መኖሪያ ውጭ ያለ ማንኛውም ግንባታ) ለመገንባት የፀደቀ ፕላን ያለው ሰው የየሥራው እርከን የሚጀምርበትን ጊዜ የሚገልጽ ማስታወቂያ የሥራ እርከኑን ከመጀመሩ 5 የሥራ ቀናት አስቀድሞ ቅጽ 025 ሞልቶ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8.2.በህንፃ መመሪያ 2/2010 አንቀጽ 16 በተዘረዘረው መሰረት ማንኛውም በምድብ "ለ" እና "ሐ" ህንጻዎች ስር የሚገኙ ግንባታዎችበተጠቀሱት የስራ እርከኖች ላይ መደበኛ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

8.3.መደበኛ ክትትል በሚደረግበት ወቅት ለክትትል የተመደበው ባለሙያ የህንፃ ግንባታ መከታተያ ቼክ ሊስት (ቼክ ሊስት 2) በመሙላት ያቀርባል፤

8.4.አንድን የህንፃ ግንባታከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እርከን ድረስ የተለያዩ ባለሙያዎች በፈረቃ ክትትል ያደርጋሉ፡፡

8.5.መደበኛ ክትትል ለማድረግ የተመደበው ባለሙያ በቀደሙት እርከኖች ላይ የተሰጡ አስተያየት ወይንም ትዕዛዞች መኖራቸውን በማጣራት ስለአፈፃፀማቸው ሪፖርት ያደርጋል፤

8.6.እንደ ሥራው ዓይነት እና የአሠራር ዘዴ በሕንፃ ሹሙ የሚጠየቁ ተጨማሪ እርከኖች መደበኛ ክትትል ሊደረግባቸው ይችላል፡፡

8.7.ለመደበኛ ክትትል በህንፃ መመሪያ ቁጥር 2/2010 የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል፡፡

8.8.በግንባታ ወቅት አደጋ እንዳያደርስ መወሰድ የሚገባቸው በ "ES 3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND SAFETY" መሰረት የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸው መረጋገጥ አለበት፤

9. ድንገተኛ ክትትል

9.1.ማንኛውንም በመገንባት ላይ ያለ በምድብ “ለ" እና “ሐ" የሚገኝ ሕንፃ (ከግል መኖሪያ ውጭ ያለ ማንኛውም ግንባታ) ከዚህ በታች በተዘረዘሩት እርከኖች ላይ ድንገተኛ ክትትል ይደረጋል፡-

9.1.1.ድንገተኛ ክትትል በሚደረግበት ወቅት ለክትትል የተመደበው ባለሙያ የህንፃ ግንባታ መከታተያ ቼክ ሊስት (ቼክ ሊስት 2) በመሙላት ያቀርባል፤

9.1.2.በህንፃ መመሪያ 2/2010 አንቀጽ 16 ከተዘረዘሩት እርከኖች መካከል በተመረጡ እርከኖች ላይ ባለሙያ በመመደብ ድንገተኛ ክትትል ይደረግባቸዋል፡፡

9.1.3.ድንገተኛ ክትትል ስጋትን መሰረት ባደረገ ሁኔታ በባለስልጣኑ ይደረጋል፡፡

9.1.4.የስጋት ደረጃን ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት “ከፍተኛ” ፣ “መካከለኛ” እና “ዝቅተኛ” በማለት ምደባ ይሰጣቸዋል፡፡ የስጋት ደረጃ አወሳሰን የህንጻው አገልግሎት፣ ግንባታው የሚከናወንበት ቦታ ፣ የህንጻው ዲዛይን እና በመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ በመመስረት የሚወሰን ሲሆን ያለማስታወቂያ ይከናወናል::

9.1.5.የስጋት ደረጃ ምደባቸው “ከፍተኛ” የስጋት ደረጃ ውስጥ የሚወድቁ ግንባታዎች ላይ ድንገተኛ ክትትል በማድረግ ውጤቱን ከዚህ መመሪያ ጋር ከተያያዘው በቼክ ሊስት (ቼክ ሊስት 2) መሰረት ተሞልቶ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

9.1.6.ድንገተኛ ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ የግንባታ ግብአት ናሙናዎችን ከማምረቻ ቦታዎች ወይም ግንባታ ከሚከናወንባቸው አካባቢዎች ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ ጥራታቸው እንዲረጋገጥ ያደርጋል፤ችግር በታየባቸው ላይ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እዲወሰድ ያደርጋል፤ በተጠየቀ ጊዜ ከሌሎች ተቋማትና ግለሰቦች አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ግብዓት የጥራት ምርመራ ያካሂዳል፤ ውጤቱን ያሳውቃል፤

9.2.ለድንገተኛ ክትትል ማስታወቂያ መጠየቅ የማያስፈልግ ሲሆን ክፍያ አይከፈልም፡፡

10. ግንባታ ቁጥጥር

10.1.ማንኛውንም በመደበኛ ክትትል ውስጥ ያሉ ህንፃዎች በህንፃ አዋጁ፣ ደንብ፣መመሪያእና በተፈቀደላቸው የግንባታ ፈቃድ መሰረት እየተገነባ ስለመሆኑ ቁጥጥር ይደረጋል፡፡

10.2. በገንቢው ስም ፋይል ተከፍቶ የተሟላ መረጃ ሰለመኖሩ ያጣራል፤ መረጃ ተደራጅቶ ካልተያዘ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

10.3.ማንኛውንም በመደበኛ ክትትል ውስጥ ያሉ ህንፃዎች በህንፃ አዋጁ፣ ደንብ፣መመሪያ መሰረት እየተገነባ ስለመሆኑ ከግንባታ ፈቃድ የዲዛይን ባለሙያ እና ክትትል በሚያደርግ ባለሙያ ግንባታው በሚከናወንበት ቦታ በመገኘት በተፈቀደላቸው የግንባታ ፈቃድ መሰረት መገንባቱን ተቆጣጥሮ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

10.4.ማንኛውንም በመደበኛ ክትትል ውስጥ ያሉ ህንፃዎች በህንፃ አዋጁ፣ ደንብ፣መመሪያ መሰረት እየተገነባ ስለመሆኑየህንጻ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል፡፡

10.5.የግንባታ ቁጥጥር የሚያደርገው የግንባታ ፈቃድ ባለሙያ ወይምክትትል በሚያደርግ ባለሙያ ወይምየህንጻ ሹሙ /የተሰየመው አካል የሕንፃ አዋጁን፤ የሕንጻ ደንቡን፤ የህንፃ መመሪያ 2/2010 እና ተጓዳኝ ሕጎችንና ውሎችን በመተላለፍ የሚካሄድ ግንባታ እንዲቆም ትእዛዝ መስጠት ይችላል፡፡

10.6.ለግንባታ ቁጥጥር ማስታወቂያ መጠየቅ የማያስፈልግ ሲሆን ክፍያ አይከፈልም፡፡

ክፍል አራት፡ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

11. አጠቃላይ

11.1.ማንኛውም የሕዝብ መጠቀሚያ ህንፃ (በየትኛውም የህንፃ ምድብ ስር ቢወድቅ) የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ በህንፃ መመሪያ 2/2010 አንቀጽ 19 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት ግንባታው በፀደቀው ዲዛይን መሰረት ስለመሰራቱ ግንባታው አካል የግንባታው ቦታ ላይ በመገኘት የመጨረሻ ምርመራ ተደርጎበት ተመመርመሮ ሲረጋገጥ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

11.2.በተፈቀደው የግንባታ ፈቃድ መሰረት ክትትል የተደረገ ቢሆንም ግንባታው ከተጠናቀቀ በኂላግንባታ ላይ የዋለው ቁስ ባህሪ የአካባቢውን ነዋሪ ወይም የህንጻውን ተገልጋይ ወይም የአካካባቢውን ትራፊክ እንቅስቃሴ የሚያውክ ወይም የሚገታ ከሆነ የህንፃ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

11.3.ማንኛውም የሕዝብ መጠቀሚያ የሆነ ህንፃ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኂላ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ቼክ ሊስት (ቼክ ሊስት 3) መሰረት በመመርመር የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

11.4.የሕንፃ ሹሙ ወይም የተሰየመው አካል ደህንነቱ አስጊ አለመሆኑን ለተረጋገጠ እና በከፊል እና ሙሉ ለሙሉ ለተጠናቀቀ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

11.5.ሙሉ ለሙሉ ለተጠናቀቀ ህንፃ በህንፃ መመሪያ ቁጥር 2/2010 አንቀጽ 19.4 እንደተጠበቀ ሆኖ በተፈቀደው ዲዛይን መሰረት የማጠናቀቂያ ስራውን ለጨረሰ ህንፃ ቋሚ የመጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ክፍል አምስት፡ በህንፃ ግንባታ ወቅት መደረግ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎች

12. አጠቃላይ

12.1. ማንኛውም የሕዝብ መጠቀሚያ ህንፃ የግንባታ ሥራው ሲከናወን በህንፃ መመሪያ ቁጥር 2/2010 አንቀጽ 10 በንዑስ አንቀጽ 10.1 ላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት ግንባታው የደህንነት ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለበት፡፡

12.2. በግንባታ ወቅት ጤናን እና ድህንነትን ለማረጋገጥ በግንባታው ሂደት ላይ የሚሳተፉት በሙሉ በስራ ላይ የዋለውን የኢትዮጵያ ህንጻ ስታንዳርድ "ES 3965 OCCUPATIONAL HEALTH AND STANDARD" መሰረት ስራቸውን ማከናወን አለባቸው፡፡

12.3. የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ ወደ ስራ ከመሰማራታቸው በፊት እንደስራው አይነት መውሰድ የሚገባቸው ጥንቃቄ ተገቢውን ገንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፡፡

12.4. የፕሮጀክቱ ስራ ተቋራጭ በግንባታ ላይ የሚሳተፉ ሰራተኞች ጤናና ደህንነት ለማስጠበቅ አስፈላጊ አልባሳት ማሟላት አለበት፤አማካሪውም ይህ መሟላቱን መከታተል ይኖርበታል፤ እንዲሁም የህንጻ ሹሙም ተወካይ ሁሉም አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት፤ ያልተሟላ ከሆነ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይገባዋል፡፡

12.5. ማንኛውም ከአንድ ወለል በላይ የሚገነባ የህዝብ መጠቀሚያ ህንፃ ግንባታው ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሴፍቲ ባለሞያ ሊኖር ይገባል፤የሴፍቲ ባለሞያው የሴፍቲ ፕላን ተዘጋጅቶ በዚሁ አግባብ እየተሰራ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

ክፍል ስድስት፡ የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠርና ልዩ ልዩ

13. የተመዘገቡ ባለሙያዎችን ስለመቅጠር

በኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ስነምግባር ደንብ ቁጥር 102/2010 አንቀጽ 6 መሰረት ማንኛውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ መስራት የሚፈልግ ግለሰብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ/በፌደራል ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር መመዝገብ ይኖርበታል፤

14. የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮች ስለመቅጠር

ማንኛውም የሕንፃ ግንባታ ለማካሄድ የሚፈልግ ሰው ፈቃድ ያለውና የፈቃድ ዘመኑ የታደሰ የሥራ ተቋራጭ መቅጠር ይኖርበታል፣

15. የተመዘገቡ አማካሪዎችን ስለመቅጠር

15.1 ለማንኛውም ምድብ የሕንፃ ዓይነቶች የሚጠየቁ ዲዛይኖች ለሥራው በሚመጥኑ የተመዘገቡ አማካሪ ድርጅቶች መሠራት አለባቸው እንዲሁም ማንኛውም ግንባታ ለዲዛይን ስራ ብቻ ሳይሆን ለግንባታ ክትትል ጭምር አማካሪን በመቅጠር በአማካሪው ኃላፊነት ማሰራት አለበት፤

15.2 በአንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 15.1 መሠረት የሚቀጠሩ የዲዛይን ባለሙያዎች የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለዲዛይን እና ለቁጥጥር ሥራ ያወጣውን ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት አለባቸው፣

16. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ከዚህ በፊት ሲሰራባቸው የነበሩትን ህንጻ መመሪያ ጋር በተጨማሪነትና መመሪያውን ለማስፈፀም የወጣ ነው፡፡ የመሰረተ ልማት ቅንጅት ግንባታ ፈቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይህን ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ያሻሽላል፡፡

17. መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ከመጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ መጋቢት 2011 ዓ.ም

ትምኒት እሸቱ (አርክቴክት)
የመሰረተ ልማት ቅንጅትና የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን
ዋና ዳሬክተር

የአርክቴክቸራል ዲዛይን እርማት መስጫ መስፈርቶች(*ቼክ ሊስት 1)*

የአልሚውስም:

የግንባታውዓይነት:　　　　ፋይሉ የገባበት ቀን:

መፍቻ ፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ብቻ ምልክት ያድጉ

ተሟልቷል ?　　　- በከፊል ተሟልቷል (ማብራሪያ የሚፈልግ)

አልተሟላም X　　　-- አይመለከተውም

ክፍልአንድ:የሰነዶችምርመራናማጣራት		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
1. የሰነዶችምርመራመስፈርቶች						
1.1	***የፕላን ስምምነት እና የጊዜ ገደቡ /12 ወራት / ያላለፈ መሆኑ***					
1.2	*ዕዳና ዕገዳ ማጣሪያ እገዳ መቅረቡን /በዲዛይን ሂደት ወቅት የሚቀርብ/*					
1.3	***የግንባታ ማሻሻያ ጥያቄ ከሆነ የግንባታ ክትትል እና ቁጥጥር ሪፖርትና የመስክ ደብተር መቅረቡን***					
1.4	የዲዛይን ማፀደቂያና ማስጀመሪያ ጊዜ ገደቡን አለማለፉን (ሊዝ ወይም ሬጉላራይዝድ)					
1.5	***የተፈቀደ የቦታው አገልግሎትና የተጠየቀው የቦታው አጠቃቀም ከቀረበው ዲዛይን ጋር መመሳሰሉን***					
1.6	***ሪል ስቴት ከሆነ የአባወራ ቁጥር /በውል ተጠቅሶ ከተሰጠ/***					
1.7	የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የይሁንታ ደብዳቤ /ለኢንዱስትሪ ብቻ/					
1.8	ኢንሹራንስ /የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜ+ አንድ ዓመት/መቅረቡን					
2. የግንባታፈቃድማመልከቻቅጾች (መሙላት፣መፈረምእናማኅተም)						
2.1	***የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ መቅረቡን***					
2.2	***የፕላን ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረቢያ /ማሻሻያ ከሆነ/ መቅረቡን***					
2.3	***ጥቅል ወጪ ግምት /ህንጻው ያረፈበትን በየወለሉ በመደመር/መቅረቡን***					
2.4	***የአማካሪ ግዴታ መቅረቡን***					
2.5	የወሰንተኛ ማሳወቂያ/መግለጫ መቅረቡን					
2.6	ወሰን ላይ ለሚገነቡት የአዋሳኞች መታወቂያ ኮፒ መቅረቡን/ተቋም ከሆነ ማህተም እና ኃላፊ ፊርማ/					

3. የአማካሪውናየዲዛይንባለሙያዎችሰነድ (መፈረምእናማኅተም)		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
3.1	*የአማካሪው የታደሰ የንግድ ፈቃድ ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ፣የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምስክር ወረቀት ቅጂ፣ የግብር ከፋይ መለያ ወረቀት ቅጂ፣ የቴክኒካል ኃላፊ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የግብር ከፋይ መለያ ወረቀት ቅጂ መቅረቡን፤*					
3.2	*የባለሙያው የታደሰ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ቅጂ እና የግብር ከፋይ መለያ ወረቀት ቅጂ መቅረቡን፤*					
4. የአገልግሎት ክፍያ						
4.1	*ለአዲስ እና ለማሻሻያ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ሰነድ ሲገባ ፕላን ማስገምገሚያ መከፈሉን*					
4.2	ለአዲስ እና ለማሻሻያ የግንባታ ፈቃድ አገልግሎት ሲጠናቀቅ ፕላን ማጸደቂያ/10%/ መከፈሉን					
4.3	የግንባታ ፈቃድ ማራዘሚያ የአገልግሎት ክፍያ/25%/ በወቅቱ የዋጋ ተመን መሰረት መቅረቡን					
የባለሙያ አስተያየት: 1. **ተሟልቷል** ፡ የዲዛይን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፤ 2. **አልተሟላም:** በታሳቢነት የዲዛይን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፤ 3. **አልተሟላም:** አገልግሎት ማግኘት አይችሉም						
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					

<u>**ማስታወሻ:**</u> **በተራ ቁጥር 1.1፣ 1.3፣ 1.5፣1.6፣ 2.1፣ 2.2፣ 2.3፣ 2.4፣ 3.1፣ 3.2 እና 4.1 ላይ የተቀመጡት መስፈርቶች ካልተሟሉ ዲዛይኑ ሊመረመር አይችልም፤**

ክፍል ሁለት፡ የዲዛይን ምርመራ		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
1.Master Plan and LDP/ ከቀረበው የፕላን ስምምነት ጋር ማረጋገጥ/						
1.1	Building Height /maximum Height to be built/					
1.2	Land use					
1.3	Road Width					
1.4	FAR- Minimum and maximum					
1.5	Green Area /For every 100m2 of the plot 2m*2m					
1.6	Aviation Zone Restriction / If/					
1.7	Renewal and Strategic Area /Must have min of 10m access Road/					
1.8	Infrastructure Utility Line- electric, water, sewer, tele line and others					
1.9	River Buffer/ If/					
1.10	Social Services/ If/					
2. Site Plan						
2.1	Septic Tank location and dimension /except along the road setback from Boundaries must be 1.5m far from boundaries and 0.50m if it is shear wall and treated /					
2.2	Building Setback from Boundaries and road					
2.3	North Direction, Road name and Size					
2.4	Main entrance at least 4.00m					
2.5	Green Area /For 100m2 of the plot 2m*2m covered 1 tree/					
2.6	Roof direction and Slope in %					
2.7	Water Tanker					
2.8	Solid Waste Container Location & Garbage Chute /starting from 6 storey building/					
2.9	contour map of the building site					
2.10	Dimension of the site plan according to title deed					
2.11	CD site plan soft copy according to title deed coordinate					
2.12	Building setback up to 5m height (including Basement) shown in hidden line					
2.13	FAR and Car Parking calculation					

3. Floor Plans		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
3.1	Full Description (Floor finish, level, area, room names)					
3.2	Dimension of every doors and opening, Balcony doors					
3.3	Minimum size of the room					
3.4	Minimum Corridor and Staircase Width					
3.5	No. of Lifts Provided /Lifts above 12m height from Ground Floor/ and if stories are above 12 must be provided 2 lifts					
3.6	Size of Lift Car(Minimum 1.00m Width and 1.50m depth)					
3.7	Maximum riser and Minimum tread sizes					
3.8	Minimum flight width of staircase and corridor					
3.9	Minimum no. of Toilets for both male and female/at least 85cm width and 150cm depth/					
3.10	ventilation and light					
3.11	Minimum and maximum clear height of the floor					
3.12	Section line cutting along the main staircase					
3.13	Mention all exterior Floor plan built up area					
3.14	All floor plans title and scale					
3.15	Boundary line and setbacks from boundary and road					
3.16	Generator Room/space					
3.17	Mezzanine Floor area (≤1/3 floor Area below it					
3.18	Min and max height of mezzanine floor (2.1m-2.70m)					
3.19	Septic Tank location, dimension and setback					
3.20	Kitchen and Toilet furnishing and its functionality					
3.21	Emergency exit location and Dimension					
3.22	Green Area /For every 100m2 of the plot 2m*2m					
4. 4. Elevations(4)						
4.1	Building facade finishing material (Non reflective)					
4.3	Total height of each storey's and maximum height					
4.4	Hand rail height/Minimum 1.05m/					
4.5	Window opening percentage in relation to floor area					
4.6	Number of Floors, names, level, dimension & height					
4.7	Opening location and size; emergency exit location					

5. Section and Sectional Elevation		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
5.1	Sectional material on every floor level and roof level					
5.2	Room name of every sectional floors and clear height of the rooms					
5.3	Sectional Elevations between two blocks /if it is not seen on 4 building facades/					
5.4	Any other Detail Plan (if needed)					
6. Roof plan						
6.1	Roof Material, Slope and direction					
6.2	location of Down pipe					
6.3	Except work shop and meeting hall if it rises above 2.8m considered as a floor					
6.4	except lift and Staircase room, Terrace are considered as a floor					
7. Access for persons with Disability						
7.1	Ramp on the Ground /maximum slope must be 4.5%/					
7.2	Lift door 90cm and above, hand rail and detail					
7.3	Toilet = 1.50m diameter of clear turning area					
7.4	Location of Disabled parking /3.50mx5.00m/					
7.5	wheelchair Location (multipurpose religious halls)					
8. Fire Escape /According to the Ethiopian Standards/						
8.1	Maximum Travel distance					
8.2	No. of fire exits, exit door, corridor & lobby size					
8.3	Minimum size of exits and corridors					
8.4	Fire resistance duration					
8.5	Total occupation load					
8.6	Fire Escape Type					
9. Building Setbacks						
9.1	Setback from any Accessible Road (1m, 2m and 3m for local, CS and Sub-Arterial and Arterial Streets)					
9.2	Setbacks between two blocks for public building/refer Building Directive/					
9.3	Setbacks for windows and Opening /2m for normal and 1.5m for Top window/					
9.4	Keep blue and red line if it has on the LDP					
9.5	workshop machine setback (6m from boundary)					
9.6	Keep building Morphology if it has on the LDP					

10. Parking		በአማካሪ የሚሞላ	1ኛ	2ኛ	3ኛ	ምርመራ
10.1	Minimum standard dimension of Car Parking lot /2.50m x 5.00m/					
10.2	Minimum No. of Car parking to be provided on building type					
10.3	Minimum Room height of the car parking					
10.4	Building Depth for Parking Entrance (maximum 10% slope)					
10.5	Size of Car Lift /Minimum of 2.50m x 5.00m internal dimension /					
10.6	car access way width for two way parking minimum 5m and one way minimum 3.5m					
10.7	car entrance width at least 5m for one way and at least 3.5m for two way					
11. Title Block						
11.1	Project Title- Project Height, Status and Name					
11.2	Owner Name (according to Title Deed)					
11.3	Address- Title deed no., Sub City, Woreda, House No.,					
11.4	Client Address- Designer name, license no., and signature; Consulting Stamp					
11.5	Paper no. and Date					
የባለሙያ አስተያየት፡ 1. **ተሟልቷል** ፡ የዲዛይን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፤ 2. **አልተሟላም፡** በታሳቢነት የዲዛይን ምርመራ ማድረግ ይቻላል፤ 3. **አልተሟላም፡** አገልግሎት ማግኘት አይችሉም						
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					
	የፈጻሚው ስም ፡ ቀንና ፊርማ ፡					

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የመሠረተ ልማት ቅንጅትና
ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር
ባለሥልጣን

ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
INFRASTRUCTURE DEVELOPMENT COORDINATION AND
CONSTRUCTION PERMIT & CONTROL
AUTHORITY

ቁጥር፡ ____________

ቀን ፡ ____________

የህንፃ ግንባታ መከታተያ (ቼክ ሊስት 2)

1.አጠቃላይ መረጃ (ቢሮ ውስጥ የሚሞላ)

1.1.የባለቤቱ ስም ______________________ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ

የአካባቢ ልዩ መጠሪያ ____________ ኮኦርዲኔት X [ ] [ ]

1.2.የጉብኝቱ አይነት መደበኛ [ ] በአቤቱታ [ ] ድንገተኛ [ ]

1.3.የግንባታ ፈቃድ ቁጥር [ ] የግንባታ ፈቃድ ማብቂያ ቀን [ ]

የወለል ብዛት አጠቃላይ [ ] ከመሬት በላይ [ ] ከመሬት በታች [ ]

1.4.ግዴታ የገባው ፡ ተቋራጭ ስም____________ አማካሪ ስም ____________

1.5.የአርከኑ ስራ ከመጀመሩ ከ3 የስራ ቀናት በፊት ጥያቄ መቅረቡ (አንቀፅ 15) ቀርቧል [ ] አልቀረበም [ ]

1.6. ተገቢ የሆነ የቁጥጥር ክፍያ መደረጉን ማጣራት (አንቀፅ 21) ተከፍሏል [ ] አልተከፈለም [ ]

1.7.አስተዳደራዊ መቀጮዎችን ካለ መከፈላቸውን ማጣራት (አንቀፅ 23)

የለም [ ]

አለ ተከፍሏል [ ] አልተከፈለም [ ]

1.8. ከዚህ በፊት ያልተነሳ የማስቆሚያ ትዕዛዝ መኖሩን ማረጋገጥ አለ [ ] የለም [ ]

1.9. ከዚህ በፊት የተከታተለው ባለሙያ ስም ____________ ቅፅ ቁጥር [ ]

2. የመስክ ቁጥጥር ወቅት መታየት ያለባቸው

2.1.በግንባታ ቦታ የግንባታ ክትትል መረጃ መኖሩን ማጣራት (ደንብ፣ አንቀፅ14) አለ [ ] የለም [ ]

2.2.ተቆጣጣሪው ስለመጣበት አላማና ስለተመለከተው ሁኔታ መዝገብ ላይ መረጃ ምሙላት(ደንብ፣ አንቀፅ14)

ተሞልቷል [ ] አልተሞላም [ ]

2.3.የህንፃ አካል ለማሻሻል የፀደቀ ፕላን ሳይኖር የተሰራ ስራ(አንቀፅ14) አለ [ ] የለም [ ]

2.4.ከፀደቀው ፕላን ውጭ የተሰራ ስራ(አንቀፅ15) አለ [ ] የለም [ ]

2.5.ለሚገነባው ህንፃ የሚመጥን የተመዘገበ ተቋራጭ በስራ ላይ መኖሩን(አንቀፅ27) አለ [ ] የለም [ ]

2.6.በግንባታው የሥራ ጥራትና በጥንቃቄ ጉድለት ለሚደርሱ ጉድለቶች ዋስትና ስለመኖሩ(አንቀፅ27)

አለ [ ] የለም [ ] *(የተቋራጩን ስም ይዞ ከፋይል ላይ ማጣራት)*

2.7.በግንባታ ተቋራጩ የግዴታ መግቢያ ፎርም (ቀፅ-12) መሙላቱን ማረጋገጥ

ሞልቷል [ ] አልሞላም [ ] *(የተቋራጩን ስም ይዞ ከፋይል ላይ ማጣራት)*

3. ጥንቃቄዎች

3.1.በግንባታው አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን፣ የግንባታው ሠራተኞችን፣ የሌሎች ግንባታዎችን ወይንም ንብረቶችን በማያሰጋ መንገድ እየተገነባነው፡፡ (አንቀፅ 31) አዎ [ ] አይደለም [ ]

3.2.ከግንባታ ጋር የተያያዘ ቁፋሮ የማንኛውንም ንብረት ወይንም አገልግሎት ደህንነት ለመጠበቅ በቂ ጥንቃቄ ስለመደረጉ (አንቀፅ 31) ተደርጓል [ ] አልተደረገም [ ]

3.3.የተቆፈረው ጉድጓድ ለደህንነት አስጊ መሆን የለበትም (አንቀፅ 31) አያሰጋም [ ] ያሰጋል [ ]

3.4.ግንባታው በሕዝብ ላይ ከፍተኛ መጉላላት ማስከተሉ (አንቀፅ 32) አላስከተለም አስከትሏል

3.5.ከግንባታ ወይንም ከማፍረስ ጋር በተያያዘ የከተማው አስተዳደር ወይንም የተሰየመው አካል ንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ መጠገኛ የሚሆን ማስያዣወይንም ዋስትና መቅረብ አለበት (አንቀፅ 32)

ጉዳት አያደርስም ☐

ጉዳት ያደርሳል ☐ ዋስትና ቀርቧል ☐ አልቀረበም ☐

3.6.ማንኛውም የግንባታ ባለቤት በስራው ላይ ለሚሰማሩት ሰዎች የሚሆን ተቀባይነት ያለው የንጽህና ቦታ በግንባታው ሥፍራ ወይንምፈቃድ ከተሰጠው በሌላ ቦታ ሳያዘጋጅ ግንባታ መጀመር አይችልም።

(አንቀፅ32) ተዘጋጅቷል ☐ አልተዘጋጀም ☐

---

4. በግንባታ ወቅት የሚደረጉ ክትትሎች

4.1.ግንባታ ከመጀመሩ በፊት

4.1.1.በተፈቀደው ዲዛይን መሰረት ግንባታው ይዞታው ላይ መሆኑን ማረጋገጥ ነው ☐ አይደለም ☐

4.1.2. መንገድ የሚያዋስነው ከሆነ በሳይት ፕላኑ መሰረት set back ተጠብቋል አዎ ☐ አይደለም ☐

4.1.3. ከአጎራባች ይዞታ መራቅ ያለበት ርቀት ተጠብቋል አዎ ☐ አይደለም ☐

4.1.4. የግንባታ ዙሪያው በሚገባ ታጥሯል አዎ ☐ አይደለም ☐

4.1.5. የአፈር መከላከያ በሚገባው መሰረት ተሰርቷል አዎ ☐ አይደለም ☐

4.2.በግንባታ ወቅት

4.2.1. የህንጻ መወጣጫ (Scaffolding) አይነት የእንጨት ☐ የብረት ☐ ሌላ ________________

4.2.2. ለህንፃ ስራው የመጣውን ቁሳቁስ ጥራት ማረጋገጥ (የሚያጠራጥር ሲሆን የምርመራ ማዘዝ)

አሸዋ - የምስክር ወረቀት(ከዚህ በፊት የታዘዘ ካለ) የለም ☐ ቀርቧል ☐ አልቀረበም ☐

-ጥራት (Visual Inspection) ጥሩ ነው ☐ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ☐

ጠጠር - የምስክር ወረቀት(ከዚህ በፊት የታዘዘ ካለ) የለም ☐ ቀርቧል ☐ አልቀረበም ☐

-ጥራት (Visual Inspection) ጥሩ ነው ☐ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ☐

የሲሚንቶ - ቅዝቃዜ በማይኖርበት ቦታ ከመሬት ከፍ ብሎ ተቀምጧል አዎ ☐ አይደለም ☐

4.2.3.የፎርም ዎርክና የፎልስ ዎረክ (Form work and False work) ክትትል

- ወርድና ስፋት፣ level እና ቱንቢ (plumb) ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐
- ጠብቆ መታሰሩንና ግትርነት (Tightness & Rigidity) ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐
- ንፅህና (Cleanliness) ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐

4.2.4.የብረት ክትትል

- የብረቱ መጠንና ቁጥር (Bar Size and Nos.) ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐
- Bar Spacing & Laps ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐
- ንፅህናና ዝገት(Cleanliness and Corrosion) ትክክል ነው ☐ አይደለም ☐
- በብረቱና በፎርም ዎርኩ መሀል በቂ ክፍተት (Covers) መኖሩን አለ ☐ የለም ☐
- Hooks,Starter & Bonding Bars መኖሩን አለ ☐ የለም ☐

5.አጠቃላይ አስተያየት

ከላይ የተዘረዘሩት ቼክ ሊስቶች ከህንፃ አዋጅ፣ ደንብ እንዲሁም መመሪያዎች ጋር በማገናዘብ ግንባታው

-መቀጠል አይችሉም ☐ የግንባታ ማስቆሚያ ቁጥር ______________

-መቀጠል ይችላሉ ☐

-ከዚህ በታች የተሰጡትን እርማት በመውሰድ ከመቀጠል ይችላሉ

…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
……………………………………………

6.ተጠያቂነት

እኔ ____________________________ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ______________ ሰዓት በህንፃ አዋጁ መሰረት የቁጥጥር ስራ ለማከናወን ኃላፊነት የተሰጠኝ መሆኑን እየተገነዘብኩ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከናወን የሚገባውን ቁጥጥር ሳላከናውን በመቅረት፣ በህግ የተደነገጉትን የግንባታ ደንቦች ያልተከተለ የግንባታ ስራ ሳላስቆም የተከናወነ ወይንም የተጠናቀቀ እንደሆን በአንቀፅ 49 መሰረትተጠያቂ እንደምሆን ተረድቻለው፡፡

በተጨማሪም ማንኛውም ከግንባታ ስራ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ሰው ለመጥቀም ወይንም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይንም ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ፤ በትክክል መግለጽ ያለበትን ሁኔታ የሚያስገኘውን ውጤት ለማስቀረት ወሳኝነት ያለውን ፍሬ-ነገር ማስቀረት በአንቀፅ 51 መሠረት እንደሚያስጠይቀኝ በሚገባ ተረድቻለው፡፡

የተቆጣጣሪው ስም : ____________________________

ፊርማ : __________________

ቀን : __________________

ያፀደቀው ኃላፊ ስም : ____________________________

ፊርማ : __________________

ቀን : __________________

ቁጥር፡ ________________

ቀን ፡ ________________

የግንባታ መጠቀሚያ ፈቃድ (ቼክ ሊስት 3)

1. አጠቃላይ መረጃ (ቢሮ ውስጥ የሚሞላ)

1.1.የባለቤቱ ስም ________________________________ ክ/ከተማ ወረዳ/ቀበሌ

የአካባቢ ልዩ መጠሪያ ______________ ኮኦርዲኔት X [ ] Y [ ]

ስልክ የቢሮ ----------------------- ሞባይል -------------------------

1.2. የግንባታው አገልግሎት (በፀደቀው ፕላን የተፈቀደለት) ለ ----------------------------- አገልግሎት ነው

1.3. የግንባታ ፈቃድ ቁጥር [ ] የግንባታ ፈቃድ የተሰጠበት ቀን [ ]

1.4. የወለል ብዛት አጠቃላይ [ ] ከመሬት በላይ [ ] ከመሬት በታች

1.5. መጠቀሚያ የተጠየቀለት ግንባታ አይነት እና ደረጃው ይጠቀስ፤

ለሁሉም ይዞታ ላይ ላሉ	ይዞታ ላይ ላሉ ለሚከተሉት	ለወለል ብዛት በከፊል
____________________	____________________	____________________

2.. የመገምገሚያ ነጥቦች

2.1. የህንፃው ፊት ለፊት መግቢያ ላይ ለአካል ጉዳተኞች የተዘጋጀ ተዳፋት /ራንፕ/:

አለው [ ] **የለውም** [ ] **የተዳፋቱ መጠን በፐርሰንት (%)** [ ]

2.2. ከሳይት ፕላን አንፃር የመገምገሚያ ነጥቦች

- በተጓዳኝ የተገነቡ ጊዜያዊ ግንባታዎች **ተነስተዋል** [ ] **አልተነሱም** [ ]
- የፍሳሽ ማጠራቀሚያው ከወሰን ያለው ርቀት ጠብቆ **ተሰርቷል** [ ] **አልተሰራም** [ ]
- የንፁህ ውሀ አቅርቦት እና የፍሳሽ አወጋገድ ስርአት በተፈቀደለት መሰረት **ተሰርቷል** [ ] **አልተሰራም** [ ]
- የመጠባበቂያ ውሃ አቅርቦት /የተሰቀለ ታንከር/ **አለው** [ ] **የለውም** [ ]
- የመጠባበቂያ ኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት /ጄኔሬተር/ **አለው** [ ] **የለውም** [ ]
- የአደጋ ጊዜ ማምለጫ መወጣጫ /fire escape stair/ **አለው** **የለውም**
- ህንፃው ከወሰን ያለው ርቀት በተፈቀደለት መሰረት **ተሰርቷል** [ ] **አልተሰራም** [ ]
- ከተፈቀደው ፕላን ውጭ በይዞታው ላይ ግንባታ **የለውም** [ ] **አለው** [ ]
- በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ በይዞታው ላይ **አለው** [ ] **የለውም** [ ]
- ህንፃው ከይዞታው ያለው ርቀት ጠብቆ ተሰርቷል **ተሰርቷል** [ ] **አልተሰራም** [ ]

2.3. የቁም ገፅታ እና የቁም ገፅታ ተቆራጭ /Elevation and section / የመገምገሚያ ነጥቦች

- የህንፃው የወለል መጠን ስንት ነው? **ከመሬት በታች** [ ] **ከመሬት በላይ** [ ]
- የመስኮት ለውጥ አለው? **አለው** [ ] **የለውም** [ ]
- የውጭ ግንባታ ቁሳቁስ የማያንፀባርቅ ነው? **አለው** [ ] **የለውም** [ ]
- የቤት ቁመት ለውጥ አለው? **አለው** **የለውም**
- የገፅታ ዲዛይን ለውጥ አለው? **አለው** [ ] **የለውም** [ ]

2.4. የምድር በታች ወለል /basement floor/ የመገምገሚያ ነጥቦች

- የመኪና መግቢያ ተዳፋት /Ramp/ **አለው** ☐ **የለውም** ☐ **መጠን (%)** ☐
- የተዘጋጀው የመኪና ተዳፋት ለአገባብ እና ለመዞር ምቹ **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- ለመኪና አሽከርካዎች አንፀባራቂ ምልክቶች በወለሉና ግድግዳ ተሰርቷል ☐ **አልተሰራም** ☐
- ከተፈቀደው ፕላን ውጪ ግንባታ በወለሉ **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- ከተፈቀደው ፓላን ውጭ የወለሉን የሌላ አገልግሎት ተጠቅሟል **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- የእሳት ማጥፊ የውሃ መስመሮች ተገጥመው አገልግሎት **ይሰጣሉ** ☐ **አይሰጡም** ☐
- ለአካል ጉዳተኞች የተዘጋጀ የመኪና ማቆሚያ **አለው** ☐ **የለውም** ☐

2.5. የምድር በላይ ወለል/floors above NGL/ የመገምገሚያ ነጥቦች

- ሁሉም የመተላለፊያ ወለሎች ከማያንሸራትት የግንባታ ቁስ የተዘጋጀ **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- የሁሉም ወለል የመጸዳጃ አገልግሎት የተሟላና የሚሰራ **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- የእሳት ማጥፊ የውሃ መስመሮች ተገጥመው አገልግሎት **ይሰጣሉ** ☐ **አይሰጡም** ☐
- አሳንሰር /ሊፍት/ የተጣጣመና የሚሰራ ነው **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- እሳት መነሳት ጠቋሚ /smoke ditecter and fire alarm/ **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- ከተፈቀደላቸው ፕላን ውጭ በወለል ላይ የግንባታ ለውጥ **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- የፕላን ወለል የአገልግሎት ለውጥ **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- ሁሉም ክፍሎች በቂ የብርሃን እና አየር ማስገቢያ **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- የሁሉም ወለል ግንባታው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ነው **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- የደረጃ መወጣጫና የሰገነት /ባልኮኒ/ መደገፊያዎች ጥራቱን ጠብቆ ተሰርቷል ☐ **አልተሰራም** ☐
- የወለል የቁመት ለውጥ አለው? **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- የሜዛናይን /mezzanine/ ወለል የመጠን ለውጥ አለው? **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- ከተፈቀደው ውጭ ጫማሪ የወለል ግንባታ አለው? **አለው** ☐ **የለውም** ☐

2.6. **የግንባታው ጥቅል ይዘት**

- የግንባታው አገልግሎት አይነት በተፈቀደው መሰረት **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- ግንባታው ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ነው **ነው** ☐ **አይደለም** ☐
- ግንባታው ሙሉ በሙሉ ካልተጠናቀቀ የተጠናቀቀውና ለአገልግሎት የበቃው የወለል የትኛው ነው
  - ከመሬት በታች :______________________________
  - ከመሬት በላይ :______________________________
- የተጠናቀቀው የህንፃ ክፍል ለአገልግሎት ቢውል ከአደጋ ነፃ ነው **አለው** ☐ **የለውም** ☐
- በይዞታው ላይ ያለ ነገር ግን መነሳት ያለበት የግንባታ ቁሳቁስ አለው **አለው** ☐ **የለውም** ☐

2.7. የመተማመኛ ፊርማ

መረጃ የወሰደው ባለሞያ	የህንፃው ባለቤት ወይም ሕጋዊ ተወካይ
ስም: ______________________	ስም: ______________________
ፊርማ: ______________________	ፊርማ: ______________________

3. በዋና የህንፃው ገምጋሚ ባለሞያ የሚሞላ

3.1. በግንባታ ሳይቱ ላይ በመገኘት በተደረገው ግምገማ መሰረት የተሰጠ አስተያየት የአስተያየት አንኳር ነጥቦች፣

3.2. በዋናው የህንፃ ገምጋሚ የሚሰጥ የአስተያየት ማጠቃለያ የውሳኔ ሃሳብ

3.2.1. ከላይ በተገለፀው አንኳር የግምገማ ነጥቦች ጥቅል ውጤት መሰረት ግንባታው የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት **ይችላል** ☐ **አይችልም** ☐

3.2.2. ማንኛውም ከግንባታ ስራ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ሰው ለመጥቀም ወይንም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይንም ለሌሎች ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማስገኘት በማሰብ፤ በትክክል መግለጽ ያለበትን ሁኔታ የሚያስገኘውን ውጤት ለማስቀረት ወሳኝነት ያለውን ፍሬ-ነገር ማስቀረት በአንቀፅ 51 መሠረት እንደሚያስጠይቀኝ በሚገባ ተረድቻለው፡፡

የተቆጣጣሪው ስም : ______________________________

ፊርማ : ___________________

ቀን : __________________

ያፀደቀው ኃላፊ ስም : ______________________________

ፊርማ : ___________________

ቀን : ___________________